# የጋዳፊ ሞት ምን ትምህርት ይሰጣል?

ለጋዳፊ ሞት እንድናለቅስ ባይጠበቅም ከሞቱ ግን ተገቢውን ትምህርት መቅሰም ይጠበቅብናል፡፡ ጋዳፊ ተገንጣይ ሀይሎችን እየረዳ የኢትዮጵያን አንድነት ለአደጋ የዳረገ ከመሆኑ ሌላ የራሱን ተቃዋሚዎችን በአውሮጳና በአፍሪካ እየገደለ መቆየቱን ማስታወስ የሚገባ ነው፡፡ ጋዳፊ ከምዕራባውያን ጋር ታረቅኩ ካለ ጀምሮም በነሱው ተደግፎ ብዙ ወንጀል መፈፀሙን ቀጥሎ ነበር፡፡ ወያኔ ወደ ስልጣን በባዕዳን ተደግፎ መጓዝ ሲጀምር ለመለስ ዜናዊ ሙሉ ድጋፍን የሰጠው ጋዳፊ ነበር፡፡ ከሀዲው መለስም እኔም የመናዊ ነኝ፣ ኢትዮጵያም አረብ ናት ወደ አረብ ራቢጣ (ሊግ) እንገባለን ብሎ ቃል ሰጥቶት ነበር፡፡ ከዚያም ዋናው የሻዕቢያ ደጋፊ ሆኖ የቆየው ይኸው ገዳፊ ነው፡፡ በኤርትራ ለመሸጉት ለኦነግና ሌሎቹም 2 ሚሊዮን ዶላር የለገሰው ጋዳፊ ነበር፡፡ (ከዚህ ገንዘብ ሶሰት አራተኛውን ሻዕቢያ ለራሱ ወስዷል!) ፡፡ በዚህና ሌሎችም አቢይ ምክንያቶቸ የተነሳ ለጋዳፊ የሚለቀስ አይደለም፡፡

የጋዳፊ ሞት ግን ለሊቢያ ሕዝብ የነፃነትን ቀን የሚያበስር ነው ብሎ ማሰቡ ትልቅ ስህተት ይሆናል፡፡ የሊቢያ ሕዝብ መብትን በተመለከተ በደል ቢደርስበትም በኤኮኖሚው መስክ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ያጣ የነጣ የተራበ አልነበረም፡፡ በሊቢያ፣ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ፣ ሶሰት ሚሊዮን የሚሆኑ የውጭ ዜጎች በሰራተኝነት በልዩ ልዩ መስክ ተቀጥረው ነበር፡፡ ጋዳፊ ስልጣን ሲይዝ የጀመረውን የሀይማኖት አክራሪነት ዝንባሌም ትቶ ዛሬ ተኪዎቹ ነን የሚሉት ሊያውጁት የሚፈልጉትን የአክራሪ ሀይማኖታዊ ህግንም ባለመቀበል አገዛዙን ያስኬደ መሆኑ ደግሞ የታየ ነው፡፡ የጋዳፊ ተኪዎች ግማሾቹ እስካለፈው ጥቅምት የራሱ ሚኒስቴሮችና ባለስልጣኖች የነበሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ከአክራሪው አልቃይዳ የተያያዙና ሀገሪቷ በሻሪያ ህግ ትተዳደር ባይ መሆናቸውን ማወቅም ተችሏል፡፡ ሊቢያ ለታሊባንና አል ሸባብ መንታዎች አሳልፋ ተሰጠች ወይ የሚለው ጥያቄ መቅረቡ አልቀረም፡፡ የሊቢያን ግዙፍ የቤ.ንዚን ክምችት ለመዝረፍና ለመቀራመት እነ ፈረንሳይና እንግሊዝ ዛሬ ሲሯሯጡና ሳያፍሩም ሲለፍፉ ብንሰማም ትላንት የጣሊያኑ ቤርሉስኮኒ፣ የእንግሊዙ ቶኒ ብሌይርና የፈረንሳዩ ሳርኮዚ ጥብቅ የጋዳፊ ወዳጅ ነን ብለው ሲጮሁ ተደምጠዋል፡፡ ውስጠ አዋቂዎች በግንጠላ አፍቃሪዋ ቤንጋዚ የተጀመረውን ፀረ ጋዳፊ እንቅስቃሴ የቆሰቆሱትና ያራመዱት የምዕራባውያን የስለላ ድርጅት አባላት ናቸው ማለታቸውም መታወስ ያለበት ነው፡፡ ለማንኛውም ጋዳፊን ለመጣል በቅድሚያ የተዋደቁት ምዕራባውያን ናቸው፡፡ የአውሮጳ የጦር ቃልኪዳን ናቶ ሊቢያን ከአየር ለወራት ደብድቦና በመሬት ደግሞ ተዋጊዎቹን የሊቢያ ተወላጆች አስመስሎ ደባልቆ ያካሄደው ዘመቻ ለአፍሪካ አስፈሪ መልዕክትን ልኳል፡፡

ምዕራባውያን አፍሪካን ሲቀራመቱ ዘመን አልፏል። አዲሱ የወረራ ዘመቻ ደግሞ አንድም ፀረ ሽብርተኛ በሚል ጭምብል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የመለስ ዜናዊ ዓይነቶቹን ባንዳዎ ች አስገብሮና ተጠቅሞ የሀገር መሬትን መያዝና መበዝበዝ ነው። አፍሪካ የማዕድናትና የቤንዚንም ቋት ሆና ተገኝታለችና ቤንዚኗን ለመዝረፍ፣ማዕድኗን ለመንጠቅ፣ለም መሬቷን ለመያዝ እሽቅድምድም አለ ። ምዕራባውያን እርስ በርሳቸው (አሜሪካ፣ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ) ሲሿኮቱ በሌላ በኩል ደግሞ ምዕራባውያን በጋራ በአፍሪካ በአስፈሪ ደረጃ እየተስፋፋች ያለ ችዋን ቻይና (ና በዝቅተኛ ደረጃም ሕንድ) ጋር ይፎካከራሉ። የናይጀርን ዩራኒየም፣የምስራ ቅ ኮንጎን ኮልታንና ወርቅ፣ የጋቦንን፣ የናይጀሪያና የሱዳንን ቤንዚን፣ የኢትዮጵያን መሬት፣ ወዘተ የኔ የኔ በሚል እየተራኮቱበት ነው። ይህን ጥቅማቸውን ለማስከበርም በየቦታው በፀረ ሽብርተኛ ትግል ሽፋን ጦር አቋቁመዋል፣ የጦር ሰፈር መስርተዋል፣ ወታደርም ልከዋል፣ መለስ ዜናዊ ዓይነቶቹን ባንዳዎችንም ደግፈዋል። የአሜሪካ አቅዋምም በኦባማ ስር ዴሞክራ ሲያዊ ይሆናል ያሉንም አፍረዋል--አሜሪካ ጥቅሟን ለማስከበር ከነፍሰ ገዳዮችና መለስ ዜናዊ ዓይነት ጨፍጫፊዎች ጎን እንደምትቆምም ኦባማም አስረግጧል። በቅርቡ የአሜሪካው ኦባማ ወደ ዩጋንዳ የላካቸው 100 ብጤ ወታደሮች ማደናገሪያ ናቸው--በዩጋንዳ ራሷ በርካ ታ የአሜሪካ ወታደሮች ሰፍረው ይገኛሉ። በዩጋንዳ የቤንዚን ክምችት መገኘቱ ከዚህ ጋር በቀጥታ የተያያዘ ነው። በኢትዮጵያም እንዲሁ። የመለስ ከሀዲ አገዛዝ ለአሜሪካ የጦር አይሮፕላኖች ማረፊያ ሰፈር ለግሷል። በብላቴንና ሁርሶም የአሜሪካ ወታደሮች ስፍረዋል። የወያኔው የቀድሞ ጄኔራል ፃድቃን ከአሜሪካ መኮንኖች ጋር በመሆን ደቡብ ሱዳንን የአሜሪ ካ ለማድረግ በጁባ ከተማ ሰፍሮ እየሰራ ነው። በአሜሪካ የሚታዘዙ የወያኔ ወታደሮች በዚሁ በደቡብ ሱዳን ዬ ና ሩምቤክ በሚባሉ ቦታዎች በአሰልጣኝ ሽፋን ሰፍረዋል። ወያኔ በአሜሪካ ትዕዛዝ ወታደሮች ወደ አቤዪና ዳርፉር ልኮ ለአደጋ አጋልጧል። አሜሪካና ፈረንሳይ በጅቡ ቲ የጦር ሰፈሮች አሏቸው፣ ከ 4 ሺ በላይ ወታደሮችንም አስፍረዋል። አሜሪካ ለዩጋንዳ፣ ርዋንዳ፣ ለወያኔ፣ ፀረ ሽብርተኛ ወታደሮችን አሰልጥኗል። ከአየር በሳተላይት የሚያደርግው ን ስለላ ያቀራምታቸዋል። ነግ የሕዝብ አመፅ ቢነሳ ይህንኑ ለማፈን ዝግጅት መደረጉ ግልፅ ነው። ይህን ከግንዛቤ ያላስገባ የሕዝብ ትግል በአጓጉል ደረጃ የተዘናጋ ይሆናል።

በሊቢያ የተካሄደው ጦርነት ምዕራባውያን የአንዲትን ሀገር ሀብት ለመቆጣጠር ያካሄዱት ዘመናዊ ቅኝ አገዛዝ ጋር የተያያዘ ጦርነት ነው። ዛሬ ጋዳፊ ሞተ ቢባልም (ስለተባለም) የሊቢያም መከራ ጀመረ እንጂ አላበቃም። ተኪ የተባሉት እርስ በርሳቸው ከወዲሁ መናከስ ጀምረዋል።አክራሪ የሀይማኖት ሀጎችንም በሊቢያ ሕዝብ ላይ መጫኑ ችግር እንጂ መፍትሔ አይሆንም። ከተስፋፊ ምዕራባውያን ጋር የተቃቀፈ የሊቢያ አገዛዝም ለአፍሪካ መርገም

ነው። ጋዳፊ አነሰም በዛም የአፍሪካ ህብረት ይረጋገጥ፡ አፍሪካውያን ሀብታቸው በምዕራባው ያን አይዘረፍ ባይ በመሆኑ ይህ አቅዋሙ ለሞቱም አስተዋፅዖ አድርጓል። ሳዳም ሁሴን ላይ የተደረገው ዘመቻና ያስከተለውንም ውጥንቅጥ የምናውቀው ነው። ኢራቅ ነፃ ወጣች ያሉ አፋቸውን ገና ሳያብሱ ያሉትን መልሶ መዋጥ ተገደዋል። የኢራቅን ቤንዚንና ሀብት ለመቆ ጣጠር የተደረገው ጦርነት መዘዙ ገና አላበቃም። ከዚህም ሆነ ከሊቢያው ጦርነት የምንማረ ው ሀቅ ምዕራባውያን ጥቅማቸውን ለማስከበር የአፍሪካ ሀገሮችን በሀይል እየወረሩና በባንዳዎ ች እየተጠቀሙ የነፃነት ትግሎችን ለማፈንና የማይፈልጓቸውንም ለማስወገድ ዕቅድ አውጥ ተው መነሳታቸውን ነው። ፈረንሳይ በአይቮሪ ኮስት ያደረገችው የሀይል ጣልቃ ገብነት ሌላ ምሳሌ ነው። የምዕራባውያን ወዳጅ የሆነ ፀረ ሕዝብ አምባገነን ማንንም ሳይፈራ ሕዝብን እየፈጀም ቢሆን መቀጠል ይችላል ነው መልዕክቱ ። ምሳሌ ከተባለ  መለስንም፤የጅቡቲንም ገሌህ ሆነ የዩጋንዳውንም መሪ ይጠቅሷል። ከአሜሪካና ከምዕራባውያን የተጣላ ግን ውርጅብ ኙ መዓት ይሆናል። ጋዳፊም ሆነ ሙጋቤ ከሕዝብ መብት አንፃር ያደረሱት በደል ከመለስ ዜናዊ ጋር የሚወዳደር አይደለም። በአፍሪካ ምድር 35 ሺ የፖለቲካ እስረኞችን አፍኖ የያዘ ፤ጨካኝና ዘግናኝ ስየል በእስረኞች ላይ እያካሄደ ያለው ወያኔ ነው። ፀያፍ ዘረኝነት የወያኔ መለያ ነው። ግን የአሜሪካና እንግሊዝ ወዳጅ ነው። ምዕራባውያን ሆኑ ቻይናውያን ወይም መሬታችንን እየያዙና እየተቀራመቱ ያሉ አረቦች የመለስን ዕድሜ ለማራዘም አሊያም እሱ ን በሌላ ወያኔ ለመተካት ያስባሉ እንጂ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ መንግስት እንዲ መጣ አይፈልጉም። ይህ አፍሪካን ሁሉ በተመለከተ ሀቅ ነው። ከሊቢያ ቤንዚን ልንቀዳ መጀመራችን ነው ብሎ ሳያፍር የፈረንሳይ መንግስት የሚፈነድቀው የጥቃቱ ነገር ዓለሙና ውስጠ መስጢሩ የተጋለጠ በመሆኑ ነው። ለሀብቷ ሲባል አፍሪካ ትደበደባለች፤ ትጠቃላች፤ ትወረራለች። ለዚህም ነው መወጣጫ የሚሆነውን የባንዳ ቡድን በፍጥነት ማስወገድና ለእበላ ባዮችና የምዕራቡ ቅጥረኞች መንገዱን ሁሉ ዝግ ማድረግ የሚገባው።

ጋዳፊ ወደቀ ወይም ሞተ ብለን ከበሮ የማንደልቀው ድሉ የሊቢያ ሕዝብ ሳይሆን የፀረ ሊቢያና ፀረ አፍሪካ ሀይሎች በመሆኑ ነው።